# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 189 ታህሳስ 19 2004 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የመለስ ዜናዊ የይስሙላ ችሎት በስዊድናዊያን ጋዜጠኞች ማርቲን ሽብየ እና ጆአን ፐርሰን ላይ የጥፋተኝነት ብይን ከሰጠ በኋላ እያንዳንዳንዳቸውን በአስራ አንድ ዓመታት ጽኑ እስራት መቅጣቱ መላውን ዓለም አስቆጥቷል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄም እነዚህን የመለስ ዜናዊ የይስሙላ ችሎት ውሳኔዎችን አጥብቆ ያወግዛል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ታማኝነታቸው እየመነመነ የመጣ ባለ ከፍተኛ ማዕረግ የጦር አባላትን በጡረታ አባረረ። አብዛኞቹ ተባራሪዎች የሌሎች ብሔረሰብ አባላት መሆናቸው ታወቀ

የወያኔ መከላከያ ሚንስቴር ሰሞኑን ይፋ ባደረገው ዜና በወያኔ የመተካካት ፖሊሲ በመከላኪያ ሠራዊት ውስጥ ካሉት ከፍተኛ ባለማዕረጎች ውስጥ 13 ጀኔራሎችና 303 ሌፍቴናንት ኮሌነልነትና ሙሉ ኮሌነል ማዕረግ ያላቸው አባላት በጡረታ ስም ከሰራዊቱ መገለላቸው ታውቆአል።

የግንቦት7 ምንጮች መረጃ እንደሚያመለክተው ግን በጡረታ ከተገለሉት አብዛኞቹ ከቀርብ ጊዜያቶች ወዲህ በመላው አገሪቱ ውስጥ በተከሰተው የኑሮ ውድነትና እየተስፋፋ በመጣው የፖለቲካ አፈና ምክንያት ህዝባዊ አመጽ ቢቀሰቀስ ከአገዛዙ ጎን መቆማቸው ጥርጣሬ ውስጥ የገባ ባለማዕረጎችን ከሰራዊቱ ውስጥ አስቀድሞ ለማስወገድ የተወሰደ እርምጃ እንደሆ ነው።

በሰራዊቱ ውስጥ የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን ያለውና በዕድሜም ቢሆን ከአብዛኛዎቹ ተሰናባቾች በአንጋፋነት ላይ ካለው ሳሞራ ዩኑስ ጋር በፈጠሩት ግጭት ለመለስ ዜናዊ ቡድን ታማኝ መሆናቸው ጥርጣሬ ውስጥ በመግባቱ ከሰራዊቱ ውስጥ ገለል እንዲሉ ከተፈለጉት ጥቂት የትግራይ ተወላጆች በስተቀር አብዛኞቹ ተሰናባቾች የአማራ፤ የኦሮሞና የሌሎች ብሄረሰብ ተወላጆች እንደሆኑ የሚናገሩ ምንጮች፤ ትግርኛ ተናጋሪዎቹ ወደሌላ ሲቪል መሥሪያ ቤትና በህወሃት ሥር በሚተዳደሩ ንግድ ድርጅቶች ለእስከዛሬው አገልግሎታቸው እና ህወሃት ለሁለት በተከፈለበት ወቅት ድጋፋቸውን ለመለስ ቡድን በመስጠት እንዲያንሰራራ በማድረግ ላበረከቱት ውለታ የሚመጥን ሹመት እንደተዘጋጀላቸው ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በዳርፉር አመጽያን መሪ ግድያ ዙሪያ የወያኔ እጅ ሳይኖርበት እንደማይቀር ተዘገበ። መለስ ዜናዊ የኤርትራውን ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂን የማስገደል ዕቅድ እንዳለው ተጋለጠ

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት በትናትና ዜናው እንደዘገበው፤ የዳርፉር አማጺ መሪ የነበሩት ዶ/ር ካሊል ኢብራሂም ግዲያ ላይ የወያኔ እጅ ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ፍንጮች መገኘታቸውና የዘረኛው መለስ ዜናዊ አፈቀላጤ የሆነው በረከት ስሞኦን ከግዲያው አንድ ቀን ቀደም ብሎ ካርቱም ውስጥ ከሱዳን ከፍተኛ የደህንነት ሰዎች ጋር ውይይት ማድረግ መታወቁ መረጃውን የበለጠ አጠናክሮታል።

እንደኢሳት መረጃ ምንጮች ዘገባ በረከት ስሞኦን ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በአገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን ይፋ ሳይደረግ ቁጥራቸው እስከ 10 ከሚደርሱ የደህንነት አባላትና የግሉ ጥበቃ ሰዎች ጋር እንደፈረንጆች አቆጣጠር ዲሰምበር 23 ቀን በኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ሱዳን ተጎዞ ከከፍተኛ የአገሪቱ የደህንነት ሰዎች ጋር ካርቱም ላይ ምስጥራዊ የሆነ ውይይት አድርጎአል።

በረከት ስሞኦን ካርቱም ካረፈና ከአገሪቱ የደህንነት ሰዎች ጋር ውይይት ካደረገ ከሰአታት በሁዋላ የአመጽያኑ መሪ የዶ/ር ካሊል ኢብራሂም መገደል ይፋ እንደሆነ የዘገበው ኢሳት የዳርፉር አማጽያን ቃል አቀባይ የሆኑት ጂብሪል አዳም ቢላል መሪያቸው የተገደለው ከአውሮፕላን ላይ በተተኮሰ ሚሳኤል መሆኑን መግለጻቸውን ገልጾአል። የሱዳን የመከላከያ ሚኒስትር ቃል አቀባይ የሆኑት አብዱል ራሂም ሙሀመድ በበኩላቸው፣ ዶ/ር ካሊል ከአየር ላይ በተተኮሰ ሚሳኤል የተገደሉ መሆኑን አምነው፣ ግድያው የተፈጸመው ግን የስልክ ጠለፋ በማካሄድ ነው ይበሉ እንጂ ግዲያውን ለመፈጸም የአካባቢና አለማቀፍ ሀይሎች እንደተባበሩዋቸው ለቢቢሲ ዜና አግልግሎት መናገራቸው የወያኔ እጅ እንዳለበት ምንጮች ለሰጡት መረጃ ማጠናከሪያ እንደሆነ ኢሳት ዘግቦአል።

የሱዳን ትሪቢውን በትናትናው ዕለት ባወጣው ዘገባ የአማጽያኑ መሪ የተገደሉት ሰው አልባ በሆነ የጦር ጀት መሆኑንና ሁለት ጎረቤት አገሮች አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን በርካታ የአገሪቱ ጋዜጦች እንደዘገቡ ገልጾአል። የኢሳት ምንጮች እንደሚሉት ዳርፉር አካባቢ የሰፈረው የኢትዮጵያ ጦር የ ዶ/ር ካሊልን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የተመለከተ የደህንነት መረጃ ለሱዳን መንግስት አሳልፎ ሰጥቷል። ይህም ወያኔ ከሱዳን መንግሥት ልኡካን ጋር በቅርቡ ባህርዳር ከተማ ላይ አድርጎት በነበረው 14ኛው የድንበር ውይይት ወቅት (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔ ፍርድ ቤት በስዊድን ጋዜጠኞች ላይ ያስተላለፈው ቅጣት አለም አቀፍ ተቃውሞ ቀስቅሶአል

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍና ሰቆቃ ለመታዘብ ወደ ክልሉ ሲገቡ የተያዙትና በወያኔ ፍርድቤት የአስራ አንድ አመት ጽኑ እስራት የተፈረደባቸው ሁለቱ የስዊድን ጋዜጠኞች ጉዳይ ከፍተኛ የሆነ አለም አቀፍ ተቃውሞ በአገዛዙ ላይ ማስነሳቱን የዝግጅት ክፍላችን አረጋገጠ።

የወያኔ ፍርድ ቤት ከትናንት በስቲያ ባስተላለፈው ቅጣት የተቆጡና የተቃውሞ ድምጻቸውን እያሰሙ ካሉት አገሮች በተጨማሪ የተለያዩ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሚጋቾች ፍርዱን ፍትህ የሌለበት ሃሳብን በነጻ የመግለጽ ነጻነት ለመገደብ የተሰጠ የፖለቲካ ውሳኔ ሲሉ አጣጥለውታል።

የስዊድን ጠቅላይ ሚኒስትር ፍሬድሪክ ራይንፌልት መንግሥታቸው ሁለቱም ያገራቸው ዜጎች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ማንኛውንም እርምጃ እንደሚወስድ ያስታወቁ ሲሆን የአውሮጳ ህብረት የውጪ ግንኙነት ሃላፍ የሆኑት እንግሊዛዊዋ ክርስትን አሽቴን ጽቤት ባወጣው መግለጫ ሁለቱም ጋዜጠኞች በአስቸኳይ እንደሚፈቱ ያለውን እምነት ገልጾአል። ይህም በዲፕሎማሲ ቋንቋ "በአውሮጳዊያኑ ዜጎቻችን ላይ ያስተላለፋችሁት ፍርድ ውሃ የማይቋጥር ስለሆነ ጫወታችሁን ወደ ጎን ተወት አድርጋችሁ ግንኙነታችን እንዳይበላሽ ከፈለጋችሁ በአስቸኳይ ፍቱዋቸው" የሚል መልዕክት እንዳለው ለዲፕሎማቲክ ግንኙነት ቀረበታ ያላቸው ምንጮች ይናገራሉ።

የወያኔ ፍርድቤት ዳኛ የሆነው ሽምሱ ሲርጋጋ የፍርድ ውሳኔውን እያነበበ ባለበት ወቅት በብስጭት ችሎቱን ረግጠው የወጡት በኢትዮጵያ የሲዊዲን አምባሳደር ጋዜጠኛ ማርቲን ሽብየ እና ጆአን ፐርሰን ለእስር የሚያበቃ ወንጀል ያልፈጸሙ ሙያተኞች ናቸው ሲሉ መናገራቸው ይታወሳል።

ይህ በዚህ እንዳለ በጋዜጠኞቹ ላይ የተላለፈው ውሳኔ ያስቆጣቸው አትዮጵያውያን ከትናንትና በስቲያ ስቶክሆልም በሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ ፊት ለፊት የተቃውሞ ሰልፍ ማካሄዳቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን ሪፖርት ገለጸ። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ደቡብ ክልል በወያኔ ግምገማ እየተተራመሰ ነው ተባለ ። አርበኛው የኔሰው ገብሬ የከፈለውን ህይወት መስዋዕትነት ዋጋ ለማሳጣት የስም ማጥፋት ዘመቻ ያካሄደው ባለሥልጣን ከሃላፊነቱ ተባረረ። ሃያ ሰባት የመኢአድ አባላት በደቡብ ክልል በወያኔ ካድሬዎች ታሰሩ

በህወሃት የሚመራው ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በተለያየ ሹመትና ጥቅማ ጥቅሞች የራሱ ምርኮኛ አድርጎ የሚገለገልባቸውን የሌሎች ብሔረሰብ ተወላጆች በአዳዲስ ታዛዦች ለመተካት ዘወትር በሚጠቀምበት ግምገማ ሰሞኑን በደቡብ ክልል በርካታ ሰዎች ከነበሩበት የሃላፊነት ቦታ መባረራቸውን የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት በትናንትና የዜና ዘገባው አስታወቀ።

እንደ ኢሳት ዘገባ የደቡብን ክልል እያተራመሰ ያለውና ከ50 በላይ ለሚሆኑ የወያኔ የቀድሞ ሹሞች ከሃላፊነት መነሳት ምክንያት የሆነው ግምገማ ዋነኛ አላማ፤ በቅርቡ በዳውሮ ዞን በዋካ ከተማ ከተነሳው ጸረ መንግስት እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ መረጃው በአለም እንዲሰራጭ በማድረግ በኩል እጃቸው አለበት ብሎ የጠረጠሯቸውን ሹመኞቻቸውን በማባረር በአዲስ ሰዎች ለመተካት የታለመ ነው።

በአሁኑ የወያኔ ግምገማ የመባረር እጣ ከደረሳቸው ታማኝ አገልጋዮች መካከል የደቡብ ክልል የፖለቲካ ጉዳዮች ሀላፊ የነበረው አለማየሁ አሰፋ የተባለ የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት አባል አንዱ እንደሆነ የዘገበው ኢሳት ፤ በወያኔ ኢፍትሃዊነት ተማሮ በራሱ ላይ ነዳጅ በማርከፍከፍ ለህልፈት የበቃው ወጣት መምህር የኔሰው ገብሬ ዜና እንደተሰማ "የኔሰው ገብሬ የአእምሮ በሽተኛ ነበር" በማለት ሰዎች የሃሰት ምስክርነት እንዲሰጡ በማድረግ ለወያኔ አለቆቹ ከፍተኛ ዉለታ ለመዋል የሞከረ እንደሆነ ገልጾ በዚህም ምክንያት በዋካ ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ጥላቻና ተቃውሞ ከማስነሳቱም በላይ በደቡብ ክልል እየጨመረ የመጣውን የህዝብ ብሶት ለማስታገስ አልቻለም በሚል ተወንጅሎ ከተላላኪነት ስልጣኑ እንዲተባረረ ምንጮቹን ዋቤ በማድረግ ዘግቦአል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በትናትናው ዕለት ታህሳስ 16 ቀን የዳውሮ ዜን የተለያዩ ወረዳዎች ካቢኔ አባላት በዋካ ከተማ የተፈጠረውን ችግር እየገመገሙ ባሉበት ወቅት ከጌኛ ወረዳ የመጡ አርሶ አደር ራሳቸውን በገመድ ሰቅለው ለመግደል ሲሞክሩ በቦታው የነበሩ ፖሊስና የካቢኔው አባላት ባደረጉት ህይወት የማዳን ርብርቦሽ ሰውየውን ከሞት ለማትረፍ መቻሉን ኢሳት አክሎ ገልጾአል።

አርሶአደሩ ይህን እርምጃ የወሰዱት የወረዳው ካቢኔ አባል የወንድሙን ሥልጣን ጋሻ መከታ በማድረግ መሬቴን በጉልበት ቀምቶ ወስዶብኛል (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በስዊድናዊያኑ ላይ የተላለፈውን የግፍ ብይንና የቅጣት ውሳኔን እንቃወማለን፤ የኢትዮጵያዊያኑ ጉዳይ ደግሞ ያስጨንቀናል!!!

የመለስ ዜናዊ የይስሙላ ችሎት በስዊድናዊያን ጋዜጠኞች ማርቲን ሽብየ እና ጆአን ፐርሰን ላይ የጥፋተኝነት ብይን ከሰጠ በኋላ እያንዳንዳንዳቸውን በአስራ አንድ ዓመታት ጽኑ እስራት መቅጣቱ መላውን ዓለም አስቆጥቷል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄም እነዚህን የመለስ ዜናዊ የይስሙላ ችሎት ውሳኔዎችን አጥብቆ ያወግዛል።

እርግጥ ነው ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን እነዚህን የመሰሉ ፍርደ ገምድል ውሳኔዎች ለሃያ ዓመታት የኖርንበት ነውና አዲስ ነገር አይደሉም።

እንዲያውም ከዚህ ቀጥሎ ከሞላ ጎደል የሚከተሉት ኩነቶችን በቅደም ተከተላቸው እንደምናይ ከወዲሁ መገመት ይቻላል።

- ጋዜጠኞቹ ይግባኝ ከጠየቁ፤ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ያፀናል፤
- ዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቱን ያጠናክራል፤
- መለስ "በምንም ዓይነት ለውጭ ተጽዕኖ አንንበረከክም" የሚል መግለጫ ይሰጣል፤
- "የአገር ሽማግሌዎች" በጉዳዩ እንዲገቡበት ይደረጋል፤
- ስዊድናዊያኑ ጋዜጠኞች "ይቅርታ ጠየቁ" ተብሎ ይፈታሉ።

ይህ ነው የመለስ ዜናዊ ውሉ የጠፋበት ዘረኛ፣ ፊውዳላዊና ፋሽስታዊ የዳኝነት ሥርዓት።

ስዊድናዊያኑ ማርቲንና ፐርሰን እንደ ኢትዮጵያዊያኑ ጋዜጠኞች ሰቆቃ አይፈፀምባቸውም ይሆናል፤ ቢፈፀምባቸውም በኢትዮጵያዊያን ላይ እንደሚሆነው የከፋ አይሆንም። ማርቲንና ፐርሰን እንደ ርዕዮት ዓለሙ በጨለማ ቤት ለሳምንታት አይዘጋባቸው፤ እንደ እስክንድር ነጋና ውብሸት ታዩ አይረገጡ፣ አይሰደቡ፣ አይተፋባቸው ይሆናል። ያም ሆኖ ግን በኢትዮጵያዊያን ላይ እየደረሰ ያለውን ሰቆቃ በቅርበት እየታዘቡት ነው። ያዩትና የሰሙትን ሁሉ በአዕምሮዎቻቸው እየመዘገቡት ነው ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ግንቦት 7፣ እነዚህ ጋዜጠኞች እስካሁን ለከፈሉትና ወደፊትም ለሚከፍሉት መስዋትነት ከፍተኛ አክብሮት አለው። ነፃ ባለሙያዎች ናቸውና ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ መፈታት አለባቸው ብሎ ያምናል። ከዚህም ጋር ግን እንደነሱ የሚከራከርላቸውና የሚደራደርላቸው የሌላቸውን ኢትዮጵያዊያኑ ጋዜጠኞች ርዕዮት ዓለሙ፣ እስክንድር ነጋ፣ ውብሸት ታየ እና ሌሎችም እየደረሰባቸው ያለው ስቃይና መጨረሻቸው በእጅጉ ያስጨንቀዋል። ግንቦት 7፣ ኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ቁም ስቅላቸውን የሚያዩባት አገር መሆኗ እንዲያከትም በጽኑ ይታገላል።

መለስ ዜናዊና ሎሌዎቹ የመረጃን ኃይል ጠንቅቀው ያውቃሉ። በረሃ በነበሩበት ጊዜ በስውር ያስገቧቸው ጋዜጠኞች ባቀረቧቸው ዘገባዎች መጠቀማቸውን ያስታውሳሉ። እነሱ ያኔ ያደረጉትን ሌሎች ዛሬ እንዳይደግሙት መንገድ መዝጋት ይፈልጋሉ።

- ለመሆኑ እነርሱ በረሃ በነበሩበት ወቅት ምን ያህል ጋዜጠኞችን በስውር ያስገቡ እንደነበር የሚታወቅ አይመስላቸውም?
- ከእነዚህ ጋዜጠኞች ብዙዎቹ ዛሬም በሕይወት ላይ ያሉ መሆናቸውን ዘነጉት?
- አንድ ነገር ወያኔ ሲፈጽመው ሰናይ፤ ሌላው ሌላው ሲያደርገው ውግዝ የሚሆነው ለምንድነው?

ግንቦት 7 ከእንዲህ ዓይነቱን የመረጃን አፈናና የጋዜጠኞች ስቃይን ማስቆም የሚቻለው የመለስ ዜናዊን ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ አስወግደን በምትኩ ፍትህ፣ ነፃነት፣ ዲሞክራሲና እኩልነት የሰፈኑባት ኢትዮጵያን ስንገነባ ነው ብሎ ያምናል።

ስለዚህም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ ታላቅ ግብ ቆርጦ እንዲነሳ ጥሪ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ደቡብ ክልል በወያኔ ግምገማ እየተተራመሰ ነው ተባለ ። አርበኛው የኔሰው ገብሬ የከፈለውን ህይወት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ቀሬታ እንደሆነና ችግራቸውን በተደጋጋሚ ለሚመለከታቸው አካላት ቢያመለክቱም መፍትሄ የሚሰጣቸው ሰው በመታጣቱ ተስፋ ቆርጠው እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

በአገሪቱ የሰፈነው ኢፍትሃዊነት አስመርሮአቸው ህይወታቸውን ለማጥፋት ሙከራ ያደረጉ ግለሰብ በአሁኑ ጊዜ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሎአል ያለው ኢሳት መምህር የኔሰው ገብሬ ራሱን በእሳት አቃጥሎ ከገደለበት ጊዜ ጀምሮ አንድ የመንግስት ሰራተኛ ራሱን አንቆ ለመግደል መሞከሩን፣ መሬቱዋን የተቀማች ሌላ ሴት አርሶ አደር ደግሞ ገደል ውስጥ ገብታ ራሱዋን ማጥፋቱዋን የአካባቢው ነዋሪዎች ለኢሳት ገልጠዋል ብሎአል።

በሌላ በኩል በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በጎፋ ልዩ ዞን በዘንጋ አዋንዴ ቀበሌ 27 የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) አመራርና አባላት በገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ሥር መዋላቸውን መኢአድ አስታወቀ:: የደምባ ጎፋ ወረዳ ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ማዩ ማይጠሎ በበኩላቸው፣ የተጠቀሱት የመኢአድ አባላት የታሰሩት በአካባቢው እየተከናወነ ያለውን የልማት ሥራ ለማደናቀፍ በመንቀሳቀሳቸው መሆኑን ለሪፖርተር ገልጸዋል::

መኢአድ ትናንት ለሪፖርተር በላከው ጥቆማ እንዳስታወቀው፣ ታኅሣሥ 16 ቀን 2004 ዓ.ም. ከታሰሩት የመኢአድ አባላት መካከል ስድስቱ የፓርቲው አመራሮች ናቸው::

በጎፋ ልዩ ዞን የዘንጋ አዋንዴ ቀበሌ የመኢአድ ሰብሳቢ አቶ ኢልካዩ ኤሮ፣ ምክትል ሰብሳቢው መምህር አየለ ታደሰ፣ ዋና ጸሐፊው አቶ ዘሪሁን እኩሌ፣ የመኢአድ ሥራ አስፈጻሚ አባል የሆኑት አቶ ኢሳያስ ዘርቦ፣ ሃምሳ አለቃ ማናዬ ሞላልኝና አቶ መንግሥቱ ማናዬ ታኅሣሥ 16 ቀን 2004 ዓ.ም. ከቀኑ 10:00 ሰዓት አካባቢ በመኢአድ ጽሕፈት ቤት ውስጥ በስብሰባ ላይ እያሉ በፖሊሶች የታሰሩ መሆናቸውን መኢአድ አስታውቋል::

ሌሎቹ ሃያ አንድ የዘንጋ አዋንዴ ቀበሌ የመኢአድ ሥራ አስፈጻሚዎችና አባላት የታሰሩትም ከላይ በተጠቀሰው ቀን ምሽት የወረዳው የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት የመኢአድ አባላት በሚኖሩበት አካባቢ አሰሳ እንዲካሄድ ካዘዙ በኋላ መሆኑንም ገልጿል::

የዳምባ ጎፋ ወረዳ የምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ማዩ ማይጠሎ በበኩላቸው፣ የመኢአድ አባላት የታሰሩት የክልሉ መንግሥት በአካባቢው እያከናወነ ያለውን የተፋሰስ ልማት ለማደናቀፍ ሲንቀሳቀሱ በመገኘታቸው መሆኑን ለሪፖርተር ገልጸዋል::

እርሳቸው እንዳሉት፣ በደምባ ጎፋ ወረዳ የተፋሰስ ሥራ ለመሥራት ለቀያቸች ሥልጠና እየተሰጠ ጐን ለጐን ሌሎች የልማት ሥራዎች እየተከናወኑ ባሉበት በአሁኑ ጊዜ፣ ሃያ ሰባቱ የመኢአድ አባላት «የተፋሰስ ሥራውን አንሠራም» ብለው በመቃወማቸው በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ሊውሉ ችለዋል::

በአካባቢው የሚኖሩት የመኢአድ አባላት በሌሎች ቀበሌዎች የሚገኙ ነዋሪዎች በተፋሰስ ሥራው እንዳይሳተፉ የሚጠይቅ ደብዳቤ አዘጋጅተው ለመበተን ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸውን የጠቆሙት አቶ ማዩ፣ ታኅሣሥ 16 ቀን 2004 ዓ.ም. ሃያ ሰባቱ የመኢአድ አባላት ልማቱን ለማደናቀፍ ተመሳሳይ አጀንዳ ይዘው ሲወያዩ በነበረበት ወቅት በፀጥታ ኃይሎች መታሰራቸውን አረጋግጠዋል::

የመኢአድ ሥራ አስፈጻሚ አባልና የደቡብ ኢትዮጵያ ቀጣና ኃላፊ አቶ እንድሪያስ ኤሮ በበኩላቸው ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ የመኢአድ አባላት የታሰሩት ልማት በማደናቀፋቸው ሳይሆን የግለሰቦችን ማሳ አንቀፍርም ብለው በመቃወማቸው ነው::

በአካባቢው የሚገኘውን የግለሰቦች ማሳ ከመቆፈር ይልቅ ነዋሪዎች በጋራ የሚጠቀሙበትን መሬት ለተፋሰስ ሥራ ማዋል የተሻለ እንደሚሆን በመጠቆም ለቀበሌው ኃላፊዎች በጽሑፍ ጥያቄ ማቅረባቸውን የገለጹት አቶ እንድሪያስ፣ ይህ የመቃወም መብት ልማቱን እንደማደናቀፍ ተወስዶ የመኢአድ አባላት ለእስር መዳረጋቸውን አስታውቀዋል::

«የዜጎች የመናገርና የመጻፍ መብት የተጠበቀ ነው:: ተቃዋሚዎች ማንኛውንም ነገር የመቃወም መብት አላቸው፤» የሚሉት አቶ እንድሪያስ፣ የደምባ ጎፋ ወረዳ ባለሥልጣናት ግን ሕገ መንግሥቱ ለዜጐች የሰጠውን መብት በመጣስ ሰላማዊ ዜጐችን እያሰሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ::

«ዜጎች በመንግሥት ባለሥልጣናት የሚወሰኑ ውሳኔዎችን መቃወም አይችሉም ወይ?» የሚል ጥያቄ ያቀረብንላቸው የወረዳው ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ማዩ ማይጠሎ ግን፣ «ይህ የልማትና የሕይወት ጉዳይ ነው:: እነሱ ካልሠሩ ማን መጥቶ ሊሠራላቸው ነው? አንሠራም ማለት አይችሉም፤» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል:: ወረዳውም በመኢአድ አባላት ላይ «ልማትን በማደናቀፍ» በሚል ክስ ለመመሥረት እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አስታውቀዋል::

በመጨረሻም በደቡብ ክልል እየተፈጸመ ያለው ተስፋ መቁረጥ የአገሪችን ህዝብ በአገዛዙ ላይ ያለውን ምሬትና ጥላቻ ነጸብራቅ እንደሆነ ብዙዎች የፖለቲካ ተንታኞች ይስማማሉ

## የወያኔ ፍርድ ቤት በስዊድን ጋዜጠኞች ላይ ያስተላለፈው ቅጣት አለም አቀፍ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ኢትዮጵያዊያኑ ጋዜጠኞቹ በአስቸኳይ እንዲፈቱ በጠየቁበት በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በርከት ያሉ የስዊድን ታዋቂ ሚድያዎች ተገኝተው ዜናውን በሙሉ የዘገቡት ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊያን ባስተላለፉት መልእክትም በጋዜጠኛ ማርቲን ሽብየ እና ጆአን ፐርሰን ላይ የተወሰደው እርምጃ የአገራችን ዜጎች ላለፉት 20 አመታት ሲጋቱት የኖሩት ኢፍትሃዊነት መሆኑን በመረዳት ምእራባዊያን መንግስታት ወያኔን ከስልጣን ለማስወገድ የሚደረገውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል እንዲረዱ ጥሪ አቅርበዋል።

ወያኔ በጫካ ትግል ላይ በነበረበት ወቅት ይቆጣጠራቸው ወደነበሩት ቦታዎች የውጪ ጋዜጠኞችን በማስገባት ደርግ በነርሱና በአካባቢያቸው ሰላማዊ ዜጎች ላይ ይፈጽም የነበረውን ጦርነት ሲያስዘግቡ እንደነበረ ይታወቃል። የወያኔን ጸረ ደርግ ትግል ከነርሱ ጋር ሆኖ ይዘግብ ከነበሩት አንዳንዶቹ ስዊድናዊያን ጋዜጠኞች እንደነበሩ ሰሞኑን በሙሉ ባልደረቦቻቸው ላይ በተሰጠው ፍርደገምድል ውሳኔ ተቆጥተው ሲናገሩ ተደምጠዋል።

## መለስ ዜናዊ ከማንም አይሻልም!!!

መለስ ዜናዊ ከደርጉና ከአጼዎቹ ጋር ራሱን እያወዳደረ እኔ እሻላችኋለው እያለ ሲሰብክ እነሆ ሦስት አስርተ ዓመታትን አስቆጥሯል። ይሄንንም ስብከት ያመኑ ብዙ ሰዎች መኖራቸውም እውነት ነው።

መለስ ዜናዊ ዘመኑ ከደረሰበት የእደገት ደረጃ እጅግ ወደ ኋላ እርቆ የሚጓዝ ክፍ ዘረኛ በመሆኑ ሁል ግዜ ራሱን የሚያወዳድረው ከሙታን ጋር ነው እንጂ ከህያዋን ጋር አይደለም። በህያዋን መንደር የሚያቆመውን ምንም በጎ ተግባር ስላልሰራ ሙታንን ፍለጋ መቶና ሃምሳ ዓመት ወደ ኋላ ይጓዛል።

መለስ ዜናዊን ከሙታን ጋር እያወዳደሩ እርሱ ይሻላል ማለት ለማሰብ ፍላጎት ከማጣት የሚመነጭ የሞኝ ሃሳብ ነው። ለማሰብ ፍላጎት ያለው ሰው ምንም እንኳን ቀደመው የነበሩ ገዥዎች አምባገነንና ጨፍጫፊ ቢሆኑም እንደ መለስ ዜናዊ በዘረኝነት የተለከፉ አለመሆናቸውን ይረዳ ነበር።መለስ ዜናዊ ተወልደኩበት የሚለውን ብሄር "እናንተ እኮ እንደሌሎቹ ሳትሆኑ ወርቅ ናችሁ "ብሎ በአደባባይ መናገሩን ሰምተናል። ለማሰብ ፍላጎት ያለው ሰው ቀደመው የነበሩ ገዥዎች በአገሪቱ ሉዓላዊነት ላይ ከማንም ጋር እንደማይደራደሩ ማየት ይችል ነበር። በተቃራኒው ደግሞ መለስ ዜናዊ የቀደሙት ዜጎች ያቆዩልንን ድንበር እያፈረሰ ለባእዳን የመስጠቱ ጉዳይ ይከሰትላቸው ነበር። መለስ ዜናዊ በታሪክ፤ በሃይማኖትና በባህል የተሳሰረውን ወንድማማች ህዝብ በግንባር ቀደም ተዋናይነት በመለያየት በአገርና በታሪክ ላይ የፈጸመው የክህደት ወንጀል ውሎ ሳያድር የበሬ ግምባር በምታክል መሬት ላይ ትርጉም አልባ ጦርነት አስነስቶ ያስፈጀቸው ከመቶ ሺህ በላይ ወጣቶችን ክንቱ የህይወት መስዋዕትነት ያስተዋለ የሰውየውን መሰሪነት በእስካሁን ታሪካችን ከነበሩን መሪዎች ስለመሻሉ ሳይሆን ሉአላዊነታችንንና ነጻነታችንን በመግፈፍ ባሪያ ሊያደርጉን ሞክረው ካልተሳካላቸው ባዕዳን ወራሪዎች ተርታ እንደሚያሰልፈው በተገነዘቡ ነበር። የአገርን አንጡራ ሃብት በመዝረፍና በሙስና በመጨማለቅም መለስ ዜናዊን የሚስተካከል በታሪካችን ገጥሞን እንደማያውቅ ይረዳ ነበር።

መለስ ዜናዊ ክፉ ዘረኛ ነው። በአንድ አገር ህዝብ መካከል የጠብ ግድግዳ እየገነባ መኖሩ ደህና ተደርጎ የሚታወቅበት ምግባሩ ነው።ከአንድ አገር ህዝብ መካከል ተወለድኩበት የሚለውን ብሄረሰብ ጠቅሶ "አንተ እኮ እንደሌሎቹ አይደለህም ወርቅ ነህ እንጂ" ማለቱን ከአንደበቱ ሰምተናል። ይህ እንዲያው የአፍ ወለምታ ሳይሆን ሆን ተብሎ ታስቦበት የተነገር ነው። በክፉም በደጉም አብሮ ተከባብሮና ተሳስሮ የኖረ ህዝብ በአንድነት ቁሞ ስለአንድ ነገር በጋራ እንዳይመክር ለማድረግ የተጠቀመበት መሰሪ ዜዴ ነው። ከቀደሙት የአገራችን አምባገነኖች መካከል እንዲህ ያለ ነገር በአደባባይ ሲናገር የተሰማ አልታየም። ከመለስ ዜናዊ ቀድመው የነበሩ እንዲህ ያለ ነገር ቢናገሩ እንኳ ዘመኑና የነበሩበት የእድገት ደረጃ ስለሆነ የመለስ ዜናዊን ያክል የሚያሳፍርና የሚያሳስብ አይሆንም። እንዲህ ያለ ነውር ነገርን በአደባባይ ለመናገር ትንሽም ቢሆን እፍረት የማይሰማው ግለሰብ እንደምን ሁኖ ከቀደሙት ገዥዎች ሊሻል ይችላል?

እርግጥ ነው ከመለስ ዜናዊ ቀድመው በአገሪቷ ጫንቃ ላይ ተጭነው የነበሩ ገዥዎች አምባገነኖች ናቸው።እነርሱም ቢሆኑ ዴሞክራት ነን ሲሉ አልተሰሙም። ምንም እንኳ አምባገነን ቢሆኑም በአገራቸው ሉዓላዊነት ላይ ከማንም ጋር ተደራድረውና የአገሪቷን ጥቅም አሳልፈው ሲሰጡ ታይተው አይታወቁም። የአገሪቷን ዳር ድንበር አስፍተውና አስከብረው ኑረው አለፉ እንጂ እንደመለስ ዜናዊ የአገሪቷን ድንበር አፍርሰው ለባእዳን አልሰጡም።በዚህ ረገድ ቀድመው የነበሩ ገዥዎች ቢያንስ ከመለስ ዜናዊ ይሻላሉ። መለስ ከጋምቤላ አንስቶ እስከ ጎንደር ድረስ ያለውን ለም መሬት ኢትዮጵያዊ ገበሬዎችን አፈናቅሎ ለባእዳን መስጠቱ የቅርብ ግዜ ትዝታችን ነው። እንዲህ ያለ ቡድን እንደምን ሁኖ ከቀደሙት ገዥዎች ይሻላል ሊባል ይችላል?

ከመለስ ዜናዊ ቀድመው የነበሩ ገዥዎች አገሪቷ የእኔ ነች አሉ እንጂ አገራቸውን እንደ ሌላ ባእድ አገር አያዩም ነበር። መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊያን ካለው ብርቱ ጥላቻ የተነሳ "ይህች አገር" ይላል እንጂ አንድም ቀን "ወገኖቼ" ወይም ደግሞ "የተከበራችሁ የአገሬ ሰዎች" ሲል ተሰምቶ አይታወቅም። በመለስ ዜናዊ እምነት አገሪቷ የእርሱ አይደለምችም። ኢትዮጵያዊያንም ወገኖቹ አይደሉም። የእርሱ ያልሆነችን አገር በተቻለው ሁሉ ማዋረድና መዘርፍ እንጂ ክብሯን መጠበቅ መለስ ዜናዊ የተጠራበት ተልእኮው አይደለም። በዚህም መሠረት አገሪቷን እንደ አገር ሊያቆሙ የሚችሉ እሴቶችን በሙሉ ለማጥፋት ብርቱ ጥረት አድርጓል።አንዱን ሃይማኖት ከሌላው ጋር አጋጭቶ የንጹሃን ደም እንዲፈስ አድርጓል።አንዱን ብሄር የሌላው ብሄር ጠላት ነው ሲል ጽፏል ሰብኳል። በአገሪቷ ውስጥ እውነት እንዳይነገርና እንዳይለመድ አድርጓል። ዜጎችም በወንድሞቻቸውና በእህቶቻቸው ላይ በሃሰት እንዲመሰከሩ በማስገደድ ይህም በመገናኛ ብዙሃን ለህዝቡ እንዲደርስ አስደርጎ የዜጎችን ቅስም ለመስብር ጥረት አድርጓል። ቢያንስ ከመለስ ዜናዊ በፊት የነበሩ ገዥዎች በእንዲህ ያለ ነውር ውስጥ ባለመሳተፋቸው ከመለስ ዜናዊ ይሻላሉ።

የመለስ ዜናዊ አስተዳደር ከቀደሙት የሚለይበት ሌላው መልኩ ደግሞ ዝሪፊያ ነው። መለስና የኤልዛቤል መንፈስ ነች ተብላ የምትታወቀው ሚስቱ አዜብ መስፍን የአገሪቷን ሃብት በመዝረፍ ተግባር ላይ ተጠምደዋል። ይህም ዝሪፊያቸው በተባበሩት መንግስታት ሪፖርት ላይ ቀርቦ ሰምተነዋል። እስክ ዛሬ ድረስ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ከአገሪቷ ተዘርፎ በውጭ አገራት ባንክ ውስጥ የተደበቀው ገንዘብ ከአስራ አንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ሁኗል። እንዲህ ያለ ዝሪፊያ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ አይታወቅም። ይህን ዝሪፊያ የሰማ ሰው እንደምን ሁኖ መለስ ዜናዊ ከቀደሙት ገዥዎች ይሻላል ብሎ ሊናገር ይችላል ?

በአጠቃላይ አነጋገር መለስ ዜናዊ ከቀደሙት ገዥዎች ይሻላል ብሎ ይህን የዘራፊና የዘረኛ ቡድን መደገፍ ትክክል አይደለም። መለስ ዜናዊ ከቀደሙት ነገስታትና ሌሎች አይሻልም። መለስ ዜናዊ ዘረኛ፤ ውሸታምና ዘራፊ የሆነ ግለሰብ ነው። የሚመራውም ቡድን እንዲያው ነው። ከቀደሙት የሚሻልበት በጎ ነገር ሳይኖረው ይሻላል ብሎ መደገፍ አሳፋሪ ነው።እንዲህ የሚሉ ሰዎች "Animal Farm" በተባለው መጽሃፍ ውስጥ ምንም ነገር ሳያስቡ "ሁለት እግሮች ሁሉ መጥፎ፤ አራት እግሮች ሁሉ ጥሩ" እያሉ ከሚያላዝኑ በጎች የሚለዩ አይሆኑም።

ስለሆነም እያሰቡ አገሪቷንና ዜጎቿን የሚያዋርዱ ሃይሎችን ሳያስቡ መደገፍ ከተጠያቂነት የሚያስመልጥ አይደለም። ግንቦት ሰባት ሁለቱንም ሃይሎች ለይቶ አያያቸውም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## ግንቦት 7 የወያኔ ፍርድ ቤት በሁለቱ የሲውዲን ጋዜጠኞች ላይ ያስተላለፈውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማውገዝ በአስቸኳይ እንዲፈቱ የአለም አቀፍ ህብረተሰብ ጫና እንዲያደርግ ጥሪ አቀረበ

ግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሁለቱ የስዊድን ጋዜጠኞች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ያወገዘውና አለም አቀፍ ህብረተሰብ የሚችለውን ሁሉ ጫና አድርጎ ያለምንም ቅድሜ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ የጠየቀው ባለፈው ቅዳሜ ታህሳስ 15 ቀን በእንግሊዘኛ ቋንቋ ባወጣው መግለጫ ነው።

"ጋዜጠኛ ማርቲን ሽብዬ እና ጆሀን ፐርሰን ጀግኖቻችን ናቸው" በሚል ርዕስ ግንቦት 7 ባወጣው በዚህ መግለጫ፤ በህዝባዊ ወያኔ አርነት ትግራይ ቁጥጥር ሥር የሚገኘው የይስሙላ ፍርድቤት በነዚህ ሁለቱ የሲዊድን ጋዜጠኞች ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት ውሳኔ፤ በአምባገነኑ መለስ ዜናዊ የሚመራው የህወሃት ፓርቲና አገዛዙ፤ ጋዜጠኞች እውነትን በመዘገብ ህዝብ መረጃን በአግባቡ እንዲያገኝ ብሎም በመንግሥትና በህዝብ መካከል ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያደርጉ መሆናቸውን እውቅና ያልሰጠ መሆኑን ያረጋገጠ ነው ካለ በኋላ ጋዜጠኝነት ለመለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ፤ እነርሱ የሚሉትን እንደ ገደል ማምቶ ማስተጋባት ብቻ ነው ብሎአል።

መለስ ዜናዊ በትረ ሥልጣኑን ከተቆጣጠረበት 1983 ጀምሮ ነጻ ሚዲያ ላይ የተሰማሩ ጋዜጠኞችና የህተመት ውጤቶቻቸው የሥር ዓቱ ዋና የጥቃት ዕላማ ሆነዋል ያለው የግንቦት 7 መግለጫ፤ በዚህም የተነሳ በመቶዎች የሚቆጠሩት ለእስር ተዳርገዋል፤ በእስር ቤት እያሉም አሰቃቂ ሰቆቃና ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል፤ ሌሎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ደግሞ አገራቸውን ጥለው ለመሰደድ ተገደዋል፤ ይህ መግለጫ በተሰጠበት በዚህ በአሁኑ ሰዓት እንኳ በርካቶች በእስር ላይ ሁኔው ስቃይና መከራ እየተቀበሉ ነው፤ በዚህ የጭቆና ሂደት ውስጥ ለይስሙላ የተቋቋመው የፍትህ አካል ጋዜጠኞችን በመወንጀልና በእስር በመቅጣት እንደ አይነተኛ መሳሪያ እያገለገለ ይገኛል ብሎአል።

በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ እየተፈጸመ ያለውን ሰው ሰራሽ ሰቆቃ በአይናቸው ተመልከተው እውነቱን ለመዘገብ ስንቀሳቀሱ ተይዘው የታሰሩት ጋዜጠኛ ማርቲን ሽብዬ እና ጆሀን ፐርሰን ለእውነት ሲሉ ከፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈሉ ካሉ ጥቂት አለም አቀፍ ጋዜጠኞች መካከል ናቸው ያለው የግንቦት 7 መግለጫ፤ በሁለቱ ጋዜጠኞች ላይ የተፈጸመው ፍርደገምድልነት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ እውነትን ለመደበቅ ሲል በጋዘጠኞች ላይ የሚወስደው የእብሪት እርምጃ ድንበር የማያገድበው መሆኑ ያስመሰከረና ዜጎቻችን ላለፉት 20 አመታት በወያኔ ፍርድቤቶች ሲደርስባቸው የኖረውን ኢፍትሃዊነት አለም አቀፍ ህብረተሰብ እንዲያውቅ አይን ገላጭ ሆኖአል ብሎአል።

በመጨረሻም ጋዜጠኛ ማርቲን ሽብዬ እና ጆሀን ፐርሰን ሙያዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ያሳዩት ብቃትና ድፍረት በአገራቸው በስዊድን ህዝብ ፊት ብቻ ሳይሆን በኛ በኢትዮጵያዊያን ዘንድም ክብርና ሞገስ የተቸሩ ጀግና አድርጎአቸዋል በማለት አለም አቀፉ ማህበረሰብ እነዚህን ለሙያቸው ፍቅር ሲሉ በወያኔ ሰቆቃ ሥር የወደቁትን ጋዜጠኞች በአስቸኳይ ለማስፈታት የተቻላውን ሁሉ ጫና እንዲያሳርፉ ጥሪውን በማቅረብ፤ ጋዜጠኞች ከወያኔ እስር እስከፈቱ ድረስ ለሰላምና ለሰው ልጆች ነጻነት ከቆሙት ሃይሎች ጋር ቆሞ እስከመጨረሻው እንደሚፋለምላቸው ግንቦት7 በመግለጫው አረጋግጦአል።

በተያያዘ ዜና በሁለቱ ጋዜጠኞች ላይ የተወሰደው እርምጃ የስዊዲንን ህዝብና መንግሥት እጅግ ያስቆጣ መሆኑን የስዊድን ሚዲያዎች እየገለጹ ነው። የስዊድን ጠቅላይ ሚንስትር በአገራቸውና በአውሮጳ ህብረት ውስጥ ባላቸው የአባልነት መቀመጫ ስልጣን ተጠቅመው በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ተገቢውን ጫና ባለማሳረፋቸው ዜጎቻቸው በወያኔ እስር ቤት እንዲሰቃዩ ጊዜ ሰጥተዋል የሚል የሰላ ሂስ እየቀረበባቸው መሆኑ እየተዘገበ ነው።

## ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ "በለሎች እስረኞች ላይ በሃሰት መስክሪና በነጻ ትለቀቂያለሽ ተብዬ በሃሰን ሺፋና ሌሎች ወንጀል መርማሪዎች ተጠይቄ እምቢ በማለቴ ጨለማ ውስጥ ለ13 ቀናት ታግቼያለሁ" ስትል ለወያኔ ፍርድ ቤት ችሎት ተናገረች

ወጣቷ ሴት ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ ይህንን የወያኔ ከፍተኛ ወንጀል መርማሪዎች ተንኮል ያጋለጠቺው ባለፈው ሳምንት ሃሙስ የወያኔ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዴታ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት ፊት ቀርባ የተመሰረተባትን የሽብርተኝነት ክስ እንድታስተባብል በተጠየቀችበት ወቅት እንደሆነ ዘጋቢያችን ከስፍራው ከላከልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል።

ጋዜጠኛ ርዕዮት ለይስሙላ ፍርድቤቱ በሰጠቺው ማስተባበያ ቃል "እኔ በሙያዬ ጋዜጠኛ ነኝ፣ ይህን የሚያውቀው አርቲስት ደበበ እሸቱ የኢትዮጵያን ሪቪዩ ድረ ገጽ ባለቤት ጋዜጠኛ ኤልያስ ክፍሌ ሪፖርተር ሲፈልግ እኔን አገናኘው፣ እኔም ፈቃደኛ ሆንኩኝ፡፡ በዚህም ለ2 ወር ከምናምን የተለያዩ ዜናዎችን ሰርቻለሁ፡፡ መጋቢት መጨረሻ 2003 አካባቢ **በቃ** የሚል በየአካባቢው እንደተፃፈ ኤልያስ መረጃ እንዳለውና ፎቶ አንስቼ እንድልክለት ጠይቆኝ ልኬለታለሁ፡፡" ብላለች።

ርእዮት አክላም "ሌላው ፍርድ ቤቱ እንዲያውቀው የምፈልገው በርካታ መርማሪዎችና ትልልቅ ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች፣ በፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ምክትል ኮሚሽነር የሆኑት ሀሰን ሺፋ-ን ጨምሮ፣ በሌሎች ተከሳሾች ላይ በሀሰት መስክረሽ ነፃ ውጪ ብለውኛል፡፡ ይህን አልቀበልም በማለቴ እርሳቸው እንዲህ ዓይነት አቋም ካለሽ ለምን ጫካ አትገቢም ብለውኛል" በማለት ተናግራለች፡፡

ርእዮት "አንድ አሁን እዚህ ችሎት ፊት የሌለ ዐቃቤ- ሕግ፣ በሀሰት እንድመሰክር አባብሎኝ አልቀበል በማለቴ ከ25 ዓመት እስከ እድሜ ልክ እሥራት ይጠብቅሻል ብሎ ዝቶብኛል፡፡ እኔም በሰዎች ላይ በሃሰት ለመመስከር ፍቃደኛ ባለመሆኔ በማዕከላዊ እሥር ቤት ለ13 ቀናት በጨለማ ክፍል ብቻዬን አሥረውኛል፤ ከጨለማ ክፍሉ እንድወጣ በተደረኩበት ዕለትም አንዱ መርማሪ እያሳሳቀኝ አንዷ ተደብቃ በቪዲዮ ልትቀርጸኝ ሞክራ ፊቴን ከልዬ ራሴን ተከላክያለሁ በማለት የወያኔ ጀሌዎች ሊያደርሱባት ከፈለጉት የሞራልና የአካል ማሸማቀቅ እንዴት እራሷን እንዳዳነች ተናግራለች::

በመቀጠልም "እኔ ጋዜጠኛ ነኝ በሰላማዊ መንገድ መንግሥትን እቃወማለው፡፡ ይህንን በማድረጌም ሆን ብለው በኔ ላይ የሃሰት መረጃ ለማሰባሰብ ሲባል በምገለገልበት የኢሜሌ አድራሻ ከኔ ያልሆኑ በርካታ የውሸት መልዕክቶች ሆን ተበልው እንዲገቡ ተደርጎብኛል፡፡ በኢሜሌ ላይ የነ ጀሃር ሙህመድን ጽሑፍ ከተውብኝ ተጠያቂ ሊያደርጉኝ ይፈልጋሉ፡፡ የትርጉም ድርጅቱ ሁሉ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት እንዳለው በሚያስመስል መልኩ እንዲተረጉሙ በተሰጣቸው መልዕክቶች ውስጥ ሽብር ሽብር የሚል ትሩጉም ከራሳቸው ጨምረዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በሰሩት ትርጉም ውስጥ ያልነበረ አንድ ቦታ ላይ አመጽ ትክክለኛ አማራጭ ነው ብለው አቅርበዋል፡፡ ይህ ተቃዋሚ ስለሆንኩ ብቻ የተሰራብኝ ደባ ነው፡፡" ብላለች።

ይህ በዚህ እንዳለ ፍርድ ቤቱ በእነ ኤልያስ ክፍሌ የክስ መዝገብ በሽብርተኝነት ወንጀል በተከሰሱት የፖለቲካ ፓርቲ የአመራር አባል አቶ ዘሪሁን ገብረእግዚሃብሄር፣ የአውራምባ ታይምስ ምክትል ዋና አዘጋጅ ውብሸት ታዬ፣ ጋዜጠኛ ርዮት ዓለሙ እና ሂሩት ክፍሌ ላይ የመከላከያ ምሥክሮችን ባለፈው ሃሙስ አደመጠአል፡፡

አርቲስት ደበበ እሸቱ የርእዮት ዓለሙ የመጀመሪያ ተከላካይ ምሥክር ሆኖ ርዮትን ከኢትየጵያን ሪቪዩ ድረ ገጽ ጋር እንዴት እንዳገናኛቸው ለፍርድ ቤቱ ያስረዳ ቢሆንም ጋዜጠኛ ርእዮት ዓለሙ የሙያ ምሥክርነት ሊሰጡ የመጡትን የመድረክ አመራር አባልና የኦሮሞ ህዝቦች ኮንግረንስ ፓርቲ ሊቀመንበር ዶ/ር መረራ ጉዲና እና የሕግ ባለሙያ የሆኑትን ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያምን "በሕግ ላይ ሙያዊ ምስክር አይሰጥም ሕግ የመተርጎሙ ሥራ የኔ ብቻ ነው" በማለት ፍርድ ቤቱ እንዳልተቀበለ ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቶአል። ሁለቱ ምሁራን የፍርድ ቤቱን ስንብት በዝምታ ተቀብለው ሲወጡ "የቀኝ ዳኛው ችሎቱን መከታተል ከፈለጋችሁ መቀመጥ ትችላላችሁ" ሲሏቸው ዘወር ብለው በትዝብት አይን አይተዋቸው ወጥተዋል ተብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢብዴፓ) ሊቀመንበር አቶ ዘሪሁን ገብረእግዚያብሄር በበኩላቸው "እኔ የፖለቲካ ፓርቲ ሊቀመንበር ነኝ፣ ሽብርተኝነትን እናወግዛለን መቼም ቢሆን ሽብርተኝነትን ደግፈን አናውቅም፣ አንደግፍም፤ ከጋዜጠኛ ኤልያስ ክፍሌ ጋር ያለን ግንኙነት የፖለቲከኛና የጋዜጠኛ ነው፡፡ ከእርሱ የተቀበልኩት ገንዘብም ተልዕኮም የለም፡፡ ነገር ግን ለፓርቲ የሚገባ ገንዘብ ከአንድ ግለሰብ ተቀብያለሁ፣ ይህ ደግሞ በፓርቲው ሰነድ ውስጥ ይገኛል፡፡" በማለት በወያኔ የፈጠራ ክስ እንዳልተደናገጠ በሚገልጽ አነጋገር አስረድቶአል።

"ፓርቲያችን ግንቦት 20 ቀን 2003 ዓ.ም ሠላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ጥያቄ አስገብቶ ማስፈራሪያና ዛቻ ከመንግሥት ሲደርስብን ነበር፤ ፓርቲያችን የተቋቋመው መንግሥትን ለመቃወም ነው፣ በሕጉ መሠረት ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ በ24 ሰዓት ውስጥ ማሳወቅ አለበት እንጂ ማስፈቀድ አለበት አይልም፣ **መለስ በቃህ** የሚለው መፈክርም በፓርቲያችን የተፃፈ ነው፡፡ ደህንነቶች ግማሾቻችንን ደብድበውናል፣ እኔ ጸጉሬ እየተነጨ ነው የተደበደብኩት" በማለት ለፍርድ ቤቱ አሳውቋል፡፡

በኤልያስ ክፍሌ የክስ ፋይል ሦስተኛ ተከሳሽ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ዐቃቤ- ሕግ ባቀረበብኝ የስልክ፣ የኢሜል ልውውጥ ክሶች ላይ ነው የማስተባብለው አለ ካለ በሁዋላ "እኔ ሙብቴን በተጠቀምኩና ሙያዬን በመተግበሬ ነው የተከሰስኩት፣ የሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2/4 ይሄን ይፈቅድልኛል፣ ተሻሽሎ የወጣው የፕሬስ አዋጅ አንቀጽ 7 ይህን ማድረግ እንደምችል ያስቀምጣል ይሄ ይያዝልኝ" ካለ በሁዋላ ፤ "በኢሜል ልውውጡ የተጨመሩ ቃላት ወደ አማርኛ ሲተረጎም የተዛቡ ቃላት ተጨምረውብኛል፣ ይሄም ፍርድ ቤቱን ለማጭበርበር ነው፤ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሻለሁ የሚል አለ፣ ሰኔ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ኢሜል እንደተፃፃፍኩ የቀረበ አለ፣ ነገር ግን እኔ ሰኔ 12 ቀን በቁጥጥር ሥር ውዬ ሰኔ 13 ቀን ፍርድ ቤት ቀርቤያለሁ፣ እንግዲህ ከታሰርኩ ሳምንት ሆኖኝ ሁሉ ተፃፅፌያለሁ ማለት ነው፡፡ እኔ ጋዜጠኛ ነኝ ነገር ግን የጦር ጄኔራል አድርገው አቅርበውኛል፡፡ ጦርነት እየተካሄደነው የሚል አለ፡፡ ውጪ አገር ላለ ወንድሜ በእንግሊዝኛ አዛውንት አባቴ ታሞ ኦፐሬሽን ላይ ነው ይታከም ያልኩትን የጦርነት ኦፕሬሽን ነው ብለው ተርጉመውታል፡፡" ሲል የወያኔ አቃቤ ህግና ወንጀል መርማሪዎች በጋራ የሚያቀነባብሩትን የሃሰት ክስ ድራማ አጋልጦአል።

## ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ታማኝነታቸው እየመነመነ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

እንደመረጃ ምንጮቻችን መረጃ ከተባራሪዎቹ ወገን የሆኑት የአማራ የጦር መኮንኖች አብዛኞቹ ከነጀኔራል ተፈራ ማሞ ጋር የቅርብ ጓደኝነት የነበራቸው በመሆናቸው ላለፉት 3 አመታት እያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸው በህወሃት ወታደራዊ ደህንነት ክትትል ሲደረግባቸው የኖረ ነው።

መለስ ዜናዊ ለህወሃት አንጋፋ ታጋዮች ከፍተኛ የጦር መኮንንነት ማዕረግ ባደለበት ወቅት ለተለጣፊ ድርጅቶቹ በሰጠው ኮታ ከአህዴድ ለጄነራልነት ማዕረግ የበቃው ባጫ ደበሌም ከተባረሩት ጄኔራሎች መካከል አንዱ መሆኑ ታውቆአል። ባጫ ደበሌ የህወሃት አለቆቹን ተፈጥሮ በለገሰችው የዳንስ ችሎታው ያዝናና የነበረ መሆኑን በአንድ ወቅት የህወሃት የፕሬስ ሃላፊ የነበረውና ድርጅቱን ለቆ ከአገር ከወጣ ጊዜ ጀምሮ የወያኔን ወንጀሎች በማጋለጥ ሥራ ላይ የተጠመደው ደራሲ ተስፋዬ ገብረአብ ባሳተመው የደራሲው ማስታወሻ በሚባለው መጽሐፍ ለንባብ ማብቃቱ ይታወሳል።

ከተባረሩት ታዋቂ የትግራይ ጄኔራሎች መካከል በአንድ ወቅት ለመለስ ዜናዊ እጅግ ታማኝ የነበረውና በኋላ ግን ታማኝነቱ ጥያቄ ውስጥ በመግባቱ ከሳሞራ የኑስ ጋር ግጭት ውስጥ ገብቶ እንደነበር የታወቀው ዮህንስ ገብረመስቀል ይገኝበታል ተብሎአል።

መለስ ዜናዊን በመከላኪያ ሰራዊቱ ውስጥ የጀመረው ቅነሳ በትግራይ የበላይነት ምክንያት በሰራዊቱ ውስጥ ጎልቶ እየታየ ያለውን ኩርፊያና ተቃውሞ የበለጠ የሚያባብስ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የግንቦት 7 ሬዲዮ ባለፈው ቅዳሜ የዜና እወጃው የወያኔ የመከላኪያ ሚንስቴር ሚንስትር ሲራጅ ፈርጌሳ የኦሮሞ ብሄረሰብ ተወላጅ ነው ያለው በስህተት ስለሆነ የስልጤ ብሄረሰብ ተወላጅ ተብሎ አንዲስተካከል ከይቅርታ ጋር እንጠይቃለን።

## በዳርፉር አመጽያን መሪ ግድያ ዙሪያ የወያኔ እጅ ሳይኖርበት

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሁለቱም አገሮች በድንበሮቻቸው አካባቢ የምንቀሳቀሱትን የሁለቱን አገሮች አማጽያን እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የተደረሰውን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ በወያኔ በኩል የተወሰደ እርምጃ እንደሆነ የሚናገሩ የኢሳት ምንጮች፤ ሱዳን ሕልውናዋን የሚፈታተነውን የዳርፉር አማጽያን መሪ እንድትገድል ወያኔ ላደረገው ውለታ የሱዳን መንግስት የኤርትራውን መሪ ኢሳያስ አፈወርቅን ለማስገደል እንዲተባበር በበረከት ስሞዖን በኩል መጠየቋን ጠቁመዋል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ እያካሄደ ያለውን አፈናና ዘረፋ የሚያስቆም ሃይል በሱዳን መሬት በኩል እንዳይመጣበት ለመከላከል ከ1300 በላይ ርዝመት ያለው ለም የድንበር መሬታችንን በገጸ በረከትነት ለሱዳን እንዳስረከበ ሲታወቅ አሁን ደግሞ የዳርፉሩን አማጽያን መሪ በማስገደል የአልበሽሪን ወዳጅነት ለማግኘት ጎንበስ ቀና ማለቱን ቀጥሎበታል።

ተቃዋሚ ሃይሎችን ከጎረቤት አገራት ጋር በመተባበር መንቀሳቀሻና መተላለፊያ በማሳጣት አገር ውስጥ ያለውን ተቃውሞ አፍኖ የሚቀጥል እየመሰለው ያለው የወያኔ አገዛዝ ያልተረዳው ነገር ቢኖር፤ የግፍ ጽዋው ሞልቶ እየፈሰሰ ባለበት በዚህን ሰዓት ከአገረ ውስጥ ሊፈነዳ የሚችለውን እሳተ ጎሞራ ሊያስቆም ከቶ እንደማይችል የተረዳ አይመስልም የሚሉ በርካቶች ናቸው።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<ins>መካከኛ ሞገድ</ins>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<ins>አጭር ሞገድ</ins>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<ins>ማሳሰቢያ</ins>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org